# 8ኛው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በዓል በዩጋንዳ ካምፓላ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

ስምንተኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በዩጋንዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከበረ፡፡ በዓሉ በተከበረበት ወቅት በብሩንዲ፣በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ በሩዋንዳ እና በዩጋንዳ የኢፌዲሪ መንግስት ልዩ መልዕክተኛና ባለ ሙሉስልጣን ክቡር አምባሳደር ደግፌ ቡላ “ህዳር 29 ቀን የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ህገ-መንግስታችን የፀደቀበት እና የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት የሆኑበት ታሪካዊ ዕለት ነው” ብለዋል፡፡

ክቡር አምባሳደሩ በመቀጠልም ኢትዮጵያ በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም ሀይማኖቶች ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን፣ ይህንን የቆየውን እሴቶቻችንን ይዘን ልማታችንን ማፋጠን ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡ በማያያዝም ህገ-መንግሥታችን የሁሉም የሥልጣን ምንጭ እንደመሆኑ መጠን፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንደሚጠበቅበትም አሳስበዋል።

በህገ-መንግሥታችን ያገኘነውን ፖቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውጤቶችንና ቱሩፋቶችን አጠናክረን የህዳሴ ጉዞአችንን ወደማይቀለበስበት ደረጃ ለማድረስ የሁላችንንም ርብርብ እንደሚጠይቅ ገልፀው፣ እንደ ብረት የጠነከረ አንድነታችንን ለልማት በማዋል ድህነትን ለማስወገድ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በእለቱ በበዓሉ ላይ የተገኙት በዩጋንዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የመብት ጥያቄ በህገ-መንግሥቱ ምላሽ ያገኘ መሆኑንና ከእንግዲህ ወዲህ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ከሚኖሩት ኢትዮጵያውያን የሚጠበቀው ድርሻ በልማት ላይ መረባረብና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተግቶ መጠበቅ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ መንግሥት የሚያደርጋቸውን ጥረቶች እንደሚደግፉና በቀጣይም የብሄሮች፤ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን መብትና ጥቅም የሚፃረር ማንኛውንም ሁኔታ እንደሚታገሉና ለሀገር ግንባታ በጋራ እንደሚቆሙ ገልጸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዩጋንዳ የሚኖሩ የሶማሌ ክልል ተወላጆች በበኩላቸው የዘንድሮው በዓል በክልላቸው የሚከበር መሆኑንና ክልሉ ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ሰላሙ ተረጋግጦ ልማትን እያፋጠነ እንደሚገኝ ለበዓሉ ተሳታፊዎች አብራርተዋል፡፡

በዓሉ በተለያዩ አዝናኝ ሙዚቃዎች ታጅቦ የተከበረ ሲሆን በተለይም በዩጋንዳ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ተወላጆች የክልላቸውን ባህላዊ ጭፈራዎች በማሳየት በዓሉ በልዩ ድምቀት ተከብሮ እንዲውል የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ህዳር 29 ቀን 2006ዓም

የኢፌዲሪ ኤምባሲ

ዩጋንዳ-ካምፓላ